# በውሸት ደዌ ለምትሰቃዩ - እነሆ ዕውነቱን! የአፍሪካም ጭራ ነን
# (ዓለም አቀፍ ዳታዎች ምን ይላሉ?)

ሲሣይ አጌና /አዲስ አበባ/

ከአምስት ዓመት በፊት 1997 ኢትዮጵያ ዲሞክራሲን አማጠች፣ የተስፋ ብርሃንም ተንቦገቦገ፤ኢትዮጵያ ሚያዚያ 30 የጀመራትን ምጥ ግንባት 7/97 ተገላገለች፣ዲሞክራሲም ተወለደ፤ ግንቦት 7 አመሻሹ ላይ ሕፃኑ ዲሞክራሲ ሕመም ጀመረው፣ በማግስቱም ሕመሙ ፀናበት፤ ሕፃኑ አንዴ እየተሻለው ሌላ ጊዜ ደግሞ እየበ ረታበት ግንቦት 29 ሕመሙ አጣደፈው፣ ግንቦት 30 ይበልጥ በረታበት፤ ሰኔ 1 ቀን ነፍሱ አልወጣ አለች እንጂ በድን ሆነ፤ አዎን ሕፃኑ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲ በ«ኮማ» (ሠመመን) ውስጥ ለአራት ወራት ያህል ቆይቶ ጥቅምት 22/1998 አሸለበ፤ ሁሉም ነገር ወደ ኋላ ተመለሰ፡፡ ኢትዮጵያ ወደ ኋላ እየሮጠች ዓመቱ ወደፊት እየገሠገሠ እነሆ 2002 ደረሰ፤ጥቂቶች በተስፋ election ሚጠብቁ ሁሉ ነገር በ selection ተደመደመ፡፡

የኢትዮጵያ ጨቅላው ዲሞክራሲ መቃብር ወርዶ ሀውልት ቆሞለታል በሚለው ላይ በተቃውሞው ጎራ የተሰለፈውንና በገለልተኝነት የቆመውን ሁሉ በአንድ አቋም ባያስማማም ዲሞክራሲያዊ ሂደቱ በክፉ ደዌ ተይዞ ጣእር ላይ ስለመሆኑ በዚህ ሠፈር ከቶ የሚጠራጠር አልተመዘገበም፤ተቃዋሚ ስል ለአጫዋችነት የተ ሰለፉትንና ማሊያ የሚገለባብጡትን እንደማይጨምርም ማስታወሱ ተገቢ ነው፡፡በአንፃሩ ኢሕአዴግና «ገለልተኛ » ኢሕአዴጎች እንዲሁም አጫዋች «ተቃዋሚዎች» በኢትዮጵያ ዲሞክራሲው እያበበ መምጣቱን፣ኢኮ ኖሚያችንም እየተመነደገ ስለመሆኑ እየነገሩን ይገኛሉ፡፡ ደቡብ አፍሪካ፣ ጋና፣ ቦትስዋና፣ ኬፕቨርዴ፣ ሞሪሺየስ ወዘተ በርካታ የአፍሪካ ሐገራት አፍአዊ ዲሞክራሲን ተሻግረው ሠላማቸውን አረጋግጠው፣ ልማታቸውን በቁጥር ጨዋታ ሣይሆን አብዛኛው ዜጋ ኪስ በሚታይ ገንዘብ ያስመዘገቡ ሐገራት የሌላ አህጉር አካላተ እስኪመስለን ድረስ ኢትዮጵያ በዲሞክራሲ የአፍሪካ ተምሳሌት እንደሆነች ሲነገረን ሠምተናል፤ ግን ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ጥናቶች ስለጭራነታችን እንጂ ስለቀዳሚነታችን መቼ ነገሩን?

የኢትዮጵያዊያን ሕይወት ከዕለት ዕለት ቁልቁል በሚሮጥበት፣ በቀን ሶስት ጊዜ መብላት እንደ ቅንጦት እየተቆጠረ ቁርስና ምሳ ተደርበው «ቁምሣ» የሚል አዲስ ቃል በተፈጠረበት፣አንዳንዴም ቁርስ ታልፎ ምሳና ዕራት አንድነት «ምራት» የሚል ስያሜ ባገኙበት፣ ችግሩ አዳዲስ «ተርማኖሎጂ» እየፈጠረ ባለበት አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ስለመመዝገቡ ዘወትር እንሠማለን፤እርግጥ ነው ብዙሃኑ ችግር በርትቶበት በኑሮ ፈተና ተጠምዶ ከዛሬ ይልቅ ነገን በፍራቻ አሻግሮ በሚያይበት በዚህ ዘመን የደላቸው የሉም ማለት አይደለም፤ ሐብት ጋራ ላይ የወጡ፣ሞልቶ የተረፋቸውና በየባንኩኒው ገንዘብ የሚረጩ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ አቅም በኪሳቸው የሚመዝኑ አልጠፉም፡፡... ጥቂቶች በቁንጣን ተወጥረው አያሌ ሚሊዮኖች በርሃብ በሚንጠራወዙበት፣ ከዛሬው ይልቅ ስለ ነገው ጭለማ በሚፈራበት፣ ተስፋ በራቀበት ሐገር ዘወትር ስለ ኢኮ ኖሚ ዕድገት ማላዘን ከርሃቡ የበለጠ የሚያሳምም ፌዝ ነው፤ዘወትር አደግን ተብሎ የሚለፈፈው ቁጥር እውነት ቢሆን እንኳን ከሌሎች የአፍሪካ ሐገራት ጋር ሲመዘን ሐገሪቱ ያለችው በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ በመሆኑ ደረት የሚያስነፋ ሣይሆን፣ አንገት የሚያስደፋ በሆነ ነበር፡፡ ለመሆኑ የሚባለው ዕድገትስ በትክክል በእውን የሚታይ፣ በገቢር የሚገለፅ ነውን?...

በኢህአዴግ ደጋፊዎች ዘንድ ስለኢኮኖሚ ዕድገት የሚነሳው የማሣመኛ ክርክር ኢኮኖሚያችን ስለማደጉ የዓለም ገንዘብ ድርጅት /IMF/ም ምስክርነት ሠጥቶናል የሚለው ነው፤ አይ.ኤም.ኤፍ ዳታዎችን በራሱ የሚሠበሠብ ሳይሆን፣ የመንግስትን ዳታዎች መሠረት አድርጎ መረጃ የሚያቀናብር በመሆኑ መረጃ አሠባሠቡ

ጤነኛና ተዓማኒ እስካልሆነ ድረስ የ/IMF/ አደገ እያለ መውደቅ እንደሚኖርም ኢኮኖሚስቶች ያስረዳሉ፤ እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ሌላው ነጥብ ዜጎች ብቻ ሳይሆኑ ራሱ የአለም ገንዘብ ድርጅት(IMF) በኢትዮጵያ መንግስት ዳታዎች ላይ ጥርጣሬ እንዳለው ባለፈው መጋቢት ለኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት መግለጹ ነው፤በፖውል ማቲው(Paul Mathieu) የተመራውና መጋቢት 3/2002 አዲስ አበባ የገባው የአይ.ኤም.ኤፍ ልኡካን ቡድን በኢትዮጵያ ስታትስቲካዊ መረጃ የሚያቀርበው የማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ትክክለኛና የሚታመን መረጃ እንዲያቀርብ ያሳሰበ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናትም ማሳሳቢያውን ተቀብለው የመዋቅር ማስተካካያ ለማድረግ ስምምነታቸውን ገልጸዋል፤ችግሩ የአንድ ተቋም ነው ወይንስ ሕዝብን በተጋነነ አሃዝ በተስፋ ለማኖርና የውጭ ዕርዳታ ለመሰብሰብ የሚደረግ የተደራጀ መንግስታዊ ሥራ? የሚያስደነግጠው ግን ሕዝብም ለጋሾችም በሚጠራጠሩት ስታስቲክስ እንኳን የአፍሪካ ጭራ መሆናችን ነው፡፡

ሌላው በኢሕአዴግ ወገን የሚነሳው የአድገናል መከራከሪያ ዓመታዊ በጀት እየጨመረ መሄዱን ነው፤ኢኮ ኖሚስቶችም በዚህ ሐሳብ ይስማማሉ፤የበጀት ማደግ የኢኮኖሚ ዕድገት ማሳያ ስለመሆኑም ይጠቁማሉ፣ልዩነቱ ግን የኢትዮጵያ በጀት የውጭ ብድርና እርዳታን ጭምር በዋናነት መሠረት ያደረገ በመሆኑ ለዕድገት ማሳያ ሊሆን እንደማይችልም ይከራከራሉ፤በእርግጥም የኢሕአዴግ መንግስት በእርዳታና ብድር ከፍተኛ ገንዘብ የሚያገኝ ስለመሆነ አንድ አብነት ብቻ ጠቅሶ ማለፉ በቂ ነው፤ መንግስታዊው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ረቡዕ ነሐሴ 2 ቀን 1999 የገንዘብና ኢኮሚ ልማት ሚኒስቴርን ጠቅሶ ባቀረበው ዘገባ እንዳመለከተው በተጠቀሰው በጀት ዓመት (ከሐምሌ 1/1998-ሰኔ 30/1999) ሐገሪቱ 23.2 ቢሊዮን ብር እርዳታና ብድር አግኝታለች፤ከዚህ ውስጥ 15.9 ቢሊዮን ብር እርዳታ መሆኑንም ከዘገባው መረዳት ተችሏል (***ይህ ገንዘብ የአጼ ኃ/ሥላሴ መንግስት በስልጣን ዘመኑ በሙሉ ካገኘው ብድርና እርዳታ በትንሹ በሁለት ዕጥፍ ይበልጣል፤-በሌላ ጽጉፍ በዝርዝር እመለስበታለሁ***) በ2007 ኢትዮጵያ ከኤክስፐርት ምርቷ ያገኘችው 1.2 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን፣ ያስገባቸው የ4.54 ቢሊዮን ዶላር እቃዎችን ነው፤ከ3 ቢሊዮን ዶላር የሚበልጥ ልዩነት፤በኤክስፖርት የሚገኘው ገንዘብ ከነዳጅ መግዣ የማያልፍ ለመድሃኒት መግዣ እንኳን የማይተርፍ መሆኑ ሲታይ ህልውናችን ከእግዚአብሄር ቀጥሎ በምዕራባውያን ቸርነት ላይ የተመሰረተ መሆኑ ግልፅ ይሆንልናል፡፡

በ2002 የምርጫ ክርክር ወቅት የኢህአዴግ ተከራካሪዎች በምስራቅ አፍሪካ የቀዳሚ ኢኮኖሚ ባለቤት ሆነናል እስከማለት በዘለቀ ውሸት ሲጠመዱ ሥለነርሱ ሆነው ያፈሩ፣በይሉኝታ ቢስነታቸው ያዘኑ ጥቂት አልነበሩም፤የኢሕአዴግ አድገናል ልፈፋና በምስራቅ አፍሪካ የኢኮኖሚ መሪነትን የምዕራብ ሚዲያዎችም ሰምተው ተሳልቀውባቸዋል፤የእንግሊዙ ዘ ኢኮኖሚስት *(The Economist)* መፅሄት በግንቦት 22/2010 ዕትሙ የ2002 የኢትዮጵያን ምርጫ በማስመልከት «Ethiopia 's elections - five more years » በሚል ርዕስ ባቀረበው ዘገባ የአቶ መለስ መንግስት ከምርጫ 1997 በኋላ በሀገሪቱ እመቃን በማጠናከር ለ2002 ምርጫ ለራሱ መንገዱን ማደላደሉን በማስታወስ፣በምርጫ ዘመቻው ወቅት የኢኮኖሚ እድገት ስለመመዝገቡ አብዝቶ መቀስቀሱን አስፍሯል፤ነገር ግን የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ደካማ ስለመሆኑም ከኬኒያ ጋር በማነፃጸር አስቀምጧል፤ ባለፈው የፈረንጆች ዓመት ኢትዮጵያ ከውጭ ንግድ ያገኘችው የውጭ ምንዛሪ 1.4ቢሊዮን ዶላር እንደነበር አስታውሷል፤ከኢትዮጵያ በህዝብ ቁጥር በግማሽ የምታንሰው ኬንያ በተመሳሳይ ወቅት ከውጭ ንግድ ያገኘችው ከሶስት እጥፍ በላይ 5 ቢሊዮን ዶላር መሆኑንም በማስፈር ሀገሪቱ በደካማ ኢኮኖሚ ውስጥ መሆኗን አስቀምጧል፡፡ ... ኢሕአዴግ አስመዘገብኩ የሚለውን የኢኮኖሚ ዕድገት የሕዝቡ የዕለት ተዕለት ቁልቁል ሕይወትና፣ ልክ ያጣው ግሽበት ተጨባጭነቱን ወትሮውንም ጥያቄው ውስጥ ያስገቡት ከመሆናቸውም ባሻገር የተመለከትናቸውና ሌሎች ነጥቦችም፣ በራሳቸው ብዙ ይናገራሉ፤

ኢትዮጵያ አድጋለች፣ አላደገችም የሚለውን የበለጠውን ዝርዝር ለባለሙያ በመተው ለጋሾች አይታመንም ባሉት የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ መሰረት እንኳን ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ፣ በዲሞክራሲ፣ በመልካም አስተዳደር፣በኮሚኒኬሽን ወዘተ በዓለምም በአፍሪካም ያለችበትን ደረጃ በቃጣዮቹ ገፆች እንመለከታለን፤... ሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን ፣ዋርልድ ፒስ ፋውንዴሽን፣ በርትልስማን ስቲፈንግ፣ UNDP (የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ) ስቶኮልሆልም ኢንተርናሽናል ፒስ ኢንስቲቲዩት፣ ዋርልድ ጀስቲስ ፎረም ወዘተ የጥናት ውጤቶችን ለመረመረ፣ በዚህም በአንዳንድ መስኮች ከመንግስት አልባዋ ሶማልያ በታች መሆናችንን ለተመለከተ፣በኣጠቃላይ የሀገራት ጭራ መሆናችንን ላስተዋለ የኢሕአዴግ መንግስት ባለስልጣናት ይሉኝታ ቢስነት ይበልጥ ይከሰትለታል፤እድልና አጋጣሚ ሰምሮለት የውጭ እርዳታ በከፍተኛ ደረጃ እየሰበሰበ የሚገኝ መንግስት በዲሞክራሲም ፣ በልማትም በሁሉም እንዴት የአለም ጭራ ይሆናል?

መቼም አለም አቀፍና አህጉራዊ ጥናቶቹን የሚያደርጉት ተቋማትና ግለሰቦች የደርግ ሥርዓት ርዝራዦች፣የንጉሱ ሥርአት ናፋቂዎች ወይንም የሻዕቢያና የአልሻባብ ቅጥረኞች ተብለው እንደማይወነጀሉ ተ ስፋ እናደርጋለን፤አብዛኛው ሕዝብ እውነቱን የሚረዳበት መንገድ የለም በሚል ዘወትር ውሸት በመመገብ ብዙ ርቀት መሄድ አይቻልም፤ሕዝቡ ዝምታን የመረጠው የሚነገረውን ዕድገት አምኖ ተስፋ እያደረገ ሣይሆን በሀገሪቱ በሰፈነው የለየለት የጉልበት አገዛዝ ምሬት እና ብሶቱን የሚተነፍስበት ቀዳዳ በማጣቱ መሆኑንም ማስተዋሉ ተገቢ ነው። ..የተደራጀ ውሸት በመከወን የሌለውን ልማት እውን ማድረግ እንደማይቻለው ሁሉ በውሸት ስንቅ የህዝብን ልብ መግዛት አይቻልም። ይልቁንም ትርጉም የሚኖረውና ለሁሉም የሚበጀው የኢሕአዴግ መንግስት ለ19 አመታት በፖለቲካውም፣ በኢኮኖሚውም፣ በማህበራዊም መስክ ያልተሳካለትና ከአፍሪካ ሐገራት ደረጃ እንኳን ኋለኞቹ ሠፈር የተሠለፍንበት ምክንያት ምንድነው ብሎ በመጠየቅ ለመፍትሔውም መንቀሳቀስ ሲቻል ነው ። ...

ወደጥናቶቹ እናምራ፤ከላይ በተዘረዘሩት ተቋማት የተደረጉ ጥናቶችን እንዳለ በዚህ አጭር ፅሁፍ ለመዳሰስ የሚቻል አይደለም፤ምክንያቱም የአንዳንዶቹ ተቋማት ጥናት ወደ 400 ገፅ ከመሆኑ ባሻገር በአብዛኛው ተመሳሳይ በመሆኑ ይበልጥ አፍሪካ ላይ በሚያተኩሩት ሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽንና ዎርልድ ፒስ ፋውንዴሽን ላይ አተኩሬያለሁ።ከወራት በፊት የተለቀቀው የእነዚህ ተቋማት ጥናት በግንቦት 2002 የተካሄደውንና የደርግ ዘመኑን የዝሆኖች ምርጫ የሚያስታውሰውን አሳፋሪ ትርኢት አይጨምርም፤ለነገሩ እነዚህ ተቋማት በመጪው ጥቅምት ወይንም ህዳር በሚያወጡትም ሪፖርትም የግንቦቱን ምርጫ ሊሸፍኑት እንደማይችሉ ከቀደመው ሪፖርታቸው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፤የተቋማቱ ጥናት በዝርዝር እና በጥልቀት እንደ ሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ ባሉ እጅግ ስመጥር ተቋም ባለሙያዎች ስለሚሰራ ቢያንስ የአንድ አመት ክፍተት ይስተዋልበታል።

በትውልድ ሱዳናዊ በዜግነት እንግሊዛዊ የሆኑት ቢሊዬነር የዶ/ር ሞሐመድ ኢብራሂም ተቋም የሆነው ሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን በአፍሪካ ስላለው መልካም አስተዳደር ከሰሐራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ ሐገራት ላይ ያደረገውን የ2009 ጥናቱን ይፋ ሲያደርግ፣ በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥም ዋርልድ ፒስ ፋውንዴሽን የተ ባለው ተቋም ከሐሰራ በላይ የሚገኙትን 5 አረብ ሐገራትን አክሎ፣ በአጠቃላይ የ53ቱን የአፍሪካ ሐገራትን የመልካም አስተዳደር ሪፖርት ይፋ አድርጓል፤ የሁለቱም ተቋማት ሪፖርት ከ300 በሚበልጥ ገፅ የተጠናቀረ ሲሆን፣ ቀደም ሲል በጋራ አሁን ደግሞ በተናጠል ባዘጋጁት በዚህ ሪፖርት ለሐገራቱ ተቀራራቢ ደረጃዎችንና ነጥቦችን ሠጥተዋል፤ በዚህም በዲሞክራሲ የአፍሪካ ተምሳሌት እየሆነች ስለመምጣቷ፣ በኢኮሚ

ዕድገቷም ተአምር እያስመገበች ስለመሆኗ  የሚነገረን የእኛዋ ኢትዮጵያ  ከፕሮፓጋንዳው ባሻገር በባለሙያ ዎች ትንተና በሁሉም መስክ ወደ ኋላ የቀረች ብቻ ሣትሆን አሳፋሪ ደረጃ ላይ መገኘቷን እንገነዘባለን፤ በአንዳንድ መስኮች ደግሞ ላለፉት 19 አመታት መንግስት አልበ ሆና ከቀጠለችው ሶማሊያም በታች ስለመሆኗም በመረጃ የደለቡ፣ በባለሙያዎች የተነተኑ ጥናቶች አረጋግጠዋል፤ በነዚህ ሪፖርቶች መነሻነትም ሌ ሎች ወቅታዊ ሪፖርቶችንም የተመለከትኩ ሲሆን፣ ከሁሉም መረዳት የሚቻለው ዓለም ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ እየተገነዘበ ያለው፣ ኢሕአዴግ ከሚናገረው ፍፁም የተለየ መሆኑን እንረዳለን፤ በጥቅል ኢትዮጵያ ዛሬ በዓለም ላይ በሁሉም መስክ የምትገኝበት ደረጃ በጣም ዝቅ ያለ ብቻ ሳይሆን እጅግ በጣም የወረደ በመሆኑ ከ97 ምርጫ  በኋላ እየተሠሩ ያሉት ህንፃዎችና መንገዶች ሚዛኑን ሊሰቡት አልቻሉም፡፡
...እንደቀደመው ጊዜ በሐገራችን አንፃራዊወ የፕሬስ ነፃነቱ ቢኖር ኖሮ እነዚህን ሪፖርቶች ከጓደኞቼ ጋር አዘጋጃት በነበረችው «ኢትኦጵ» ጋዜጣ ላይ አትሜ የኢንተርኔት ዕድል ለሌላቸው ኢትዮጵያዊያን አንባቢያን በወቅቱ ባደረስኩኝ ነበር፤..ዛሬ በኢትዮጵያ ከሽግግር መንግስቱ ጊዜ ጀምሮ በነፃ ፕሬስ ውስጥ የቆዩ ጋዜጦች ከ1997 ምርጫ በኋላ በኢትዮጵያ ምድር እንዳይታዩ በፖለቲካ ውሳኔ ተሰርዘዋል፤...ኢህአዴግ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ የትናንቶቹን ጋዜጦች በኢትዮጵያ ምድር አያለሁ ብሎ ለማመን ኢሕአዴግ አንድ ቀን ዴሞክራሲያዊ መንግስት ሊሆን ይችላል የሚል ተስፈኝነትን ይጠይቀል፤..የእስራኤል ጠ/ሚኒስትር የነበሩት ኤርያል ሻሮን የዛሬ 5 አመት በደረሰባቸው የውስጥ የጤና እክል ከጥር 1998 ጀምሮ ራሳቸውን  እንደሳቱ አሁንም  ኮማ ውስጥ መሆናቸው ይታወቃል፤ሩህአቸው ስላልቆመ  ነፍስ ዘርተው ይነሳሉ  ብሎ የሚያምን እስራኤላዊም ሆነ የቤተሰባቸው አባል ስለሌለ «በቁማቸው» እርማቸውን አውጥተውላቸዋል፤የኢትዮጵያን ዲሞክራሲ በዚህ መልክ  ብናነፃፅር እነዚያን ፕሬሶች  በኢሕአዴግ ዘመን እናያለን ማለት፣እንደ 1997ቱ ያለ ነፃ የፖለቲካ እንቅስቃሴን ተስፋ ማድረግ ኤርያል ሻሮን ህይወት ዘርተው ይነሳሉ ብሎ የማመንን ያህል እንደተአምር ይቆጠራል፤እርግጥ ነው አሁን ባለው የህወሀት /ኢሕአዴግ  አመራር  ዲሞክራሲን መጠበቅ ኤርያል ሻሮን ይነሳሉ ብሎ እንደማመን ከባድ ቢሆንም፣በሕዝባዊና ሰላማዊ ትግል ዲሞክራሲን ዕውን እናደርጋለን ብለው ለተነሱ ዕውነተኛ ተቃዋሚዎች አክብሮቴን እገልፃለሁ፤ዕውነተኛ ስል ትግሉን መደበሪያ የሚደርጉትን አይጨምርም፡፡

ወደ ጥናቱ እንመለስ፤ኢትዮጵያ በአፍሪካ ያለችበትን የመልካም አስተዳደር ደረጃ፣ በዚህም በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማህበራዊ መስክ ያገኘችው ደረጃ በንፅፅር የተመቀጠበትን ጥናት ውጤት ዋና ዋና ነጥቦችን እንመለከታለን፤በዚህም  በጥቅል በአፍሪካ ያላትን ቦታና ከጎረቤት የአፍሪካ ቀንድ ሐገራት ጋር ያላትን ደረጃ በማነፃፀር ቀጥሎ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ ሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን ከሐሰራ በታች ባሉ 48 የአፍሪካ ሐገራት ላይ ብቻ ሲያተኩር፣ ዋርልድ ፒስ ፋውንዴሽን ደግሞ ከሰሐራ በላይ ያሉትን አረቦች ጨምሮ የ53ቱንም አፍሪካ ሐገራት በማጠቃለሉ በዚህኛው ላይ እናተኩራለን፤ከዳታዎቹና ደረጃዎቹ በፊት ጥናቱ የገለልተኛ ባለሙያ ጥናት መሆኑን ለማሳየት ጥናቱን ያካሄደው  ዋርልድ ፒስ ፋውንዴሽን /**World Peace Foundation**/ ማን ነው? የሚለውን በአጭሩ  መመለሱ ተገቢ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

## The World Peace Foundation

ዎርልድ ፒስ ፋውንዴሽን የዛሬ መቶ አመት በ1910 በቦስተን ፐብሊሸር ኤድዊን ጄን /Edwin Ginn/ ዓለም አቀፍ ሠላምና ትብብርን ለማበረታታት የተወጠነ ሲሆን፣ ይህንን ዓለም አቀፍ ትብብርና ሠላም የመሻት ዓለማውን በጥናት፣በትንታኔና በቅስቀሳ በማካሄድ ዘላቂ ሠላም የማስገኘት ሃሣብ የነበረው  ሲሆን፣ የአንደኛው የዓለም  ጦርነት ውጥኑን  ወደ ግብ እንዳይወስደው እንቅፋት ሆነ፤ሆኖም  የሠላም ፍለጋ ጥረቱ ግን

አልቀመም ነበር፤ፋውንዴሽኑ እ.አ.አ ከ1993 ጀምሮ ይበልጥ በመጠናከር በመንግስታት መካከል ያሉ ግጭቶችን የመመርመርና መፍትሔ የመፈለግ ሥራዎችንም እየሰራ ይገኛል፤ ባለፉት 10 አመታት የዓለማችን ሠላም የታወከው በዋናነት በዘር፣ በሃይማኖት፣በቋንቋ እና በማሕበረሰባዊ ጥላቻዎች እንደሆነ ፋውንዴሽኑ በጥናቱ የደረሰበት ነው።።በሩዋንዳ፣በስኒያ እና ከሳቮ የተፈፀሙ የዘር ማጥራት /Ethnic Cleansing/ ፍጅቶች ወደ ሌሎች የዓለማችን ክፍሎች እንዳይዛመቱ፣ በዚህ ዙሪያ የነበሩ አዝማሚያዎችን በእንጭጩ ለመቅጨት ፋውንዴሽኑ በኮንጐ፣ ሣይፕረስ፣ ማይናማር(በርማ)፣ ስሪላንካ፣ ሄይቲ፣ ሱዳን፣ ዚምባቡዌ ትኩረት አድርጓል፤ እንዲሁም በሁሉም አፍሪካ ሀገራት ላይ ጥናቶችን በማካሄድ አስቀድሞ ሥጋቶቻችንና መፍትሔዎችን በማመልከት በውጤት እና በውድቀት /Successes and failures/ ላይ የሚገኙ የአፍሪካ ሀገራትን የመለየት ሥራ የማሠራ መሆኑንም መረዳት ተችሏል፤

ይህ በዩ.ኤስ አሜሪካ ካምብሪጅ የሚገኘው የዓለም ሠላም ፋውንዴሽን /World Peace Foundation/ እ.ኤ.አ በ2009 መጨረሻ የአፍሪካ መንግስታትን የገመገመበትንና ደረጃ የወጣበትን ሪፖርት ይፋ አድርጓል፤ በዚህም በመልካም አስተ ዳደር ሞሪሼስ፣ ሲሼልስ፣ ኬፕ ቨርዴ እና ቦትስዋና ቀዳሚውን ስፍራ እንደ ቅደም ተከተላቸው ይዘዋል፤ በተለምዶ ከሐሰራ በታች ባሉት ሐገራት ላይ ሲያተኩር የቆየውና በዚህኛው ሪፖርቱ የሰሜን አፍሪካ ሐገሮችን ጨምሮ ሁሉንም የአፍሪካ ሐገራት ባጠቃለለው ሪፖርቱ ሞሪሺየስ ቀዳሚነቱን የያዘችው ከመቶ 86 ፐርሰንት በማግኘት ሲሆን፣ ይህም የአምስት ዘርፎች ግምገማ ድምር ውጤት ነው፤የዓለም ሠላም ፋውንዴሽን የ2007 ዳታዎችን መነሻ በማድረግ ባደ ረገው በዚህ ጥናት ዝቅተኛ ውጤት በማግኘት የመጨረሻዎ ቹ 10 ሐገራት በማለት ያስቀመጣቸው ከመጨረሻ ወደላይ ሲመዘገብ ሱማሊያ፣ ሱዳን፣ ቻድ፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኦፍ ኮንጎ፣ ኮትዲቯዋር፣ ሴንትራል አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ ኤርትራ፣ አንጎላ ዚምቧቤ እና ጊኒ ሲሆኑ፣ ጊኒን አንድ ደረጃ በመቅደም የመጨረሻዎቹ 10 ሐገራት ውስጥ ከመግባት የተፈረፈቸውና ከመጨረሻዎቹ 11 ውስጥ የምትገኘው ኢትዮጵያ ነች፤ ከኤ ርትራ፣ ሱማሊያ፣ ሱዳንና ኢትዮጵያ በስተቀር ሌሎቹ የምስራቅ አፍሪካ ሐገራት ማለትም ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ጅቡቲ በዝቅተኛው ነጥብ ውስጥ አልተመዘገቡም።

**World Peace Foundation** /የዓለም ሠላም ፋውንዴሽን/ ባደረገው ዝርዝር ጥናት ባወጣው በዚህ መረጃ ቀደመ ሲል እንደተጠቀሰው ሞሪሸስ 85.7 በማግኘት ቀዳሚ ስትሆን፣ ከ2ኛ እስከ 7ኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ከ79.8 እስከ 70.2 አግኝተዋል። ከ8ኛ እስከ 23ኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ሀገራት ደግሞ ከ69.2 እስከ 60 ነጥብ አግኝተዋል።

ከ24ኛ እስከ 40ኛ የሚገኙት ሐገራት ያገኙት ነጥብ ከ59.6 እስከ 50 ነው፤ ከ41ኛ እስከ 49ኛ የሚገኙት ሐገራት ከግማሽ በታች ያገኙ ሲሆን፣ ይህም ከ49.5 እስከ 42.7 ተ መዝግቧል፤ በተራ ቁጥር ከ50 እስከ 52 የሚገኙት ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ቻድ፣ ሱዳን ከ37.3 እስከ 34.8 ሲያገኙ፣ የመጨረሻዋ ሐገር ሶማሊያ ያገኘችው ነጥብ 16.3 ሲሆን፣ የጥናቱ ባለቤቶች በሶማሊያ ያለው የፀጥታ ሁኔታ በበቂ ሁኔታ መ ረጃ ለመሠብሠብ እንኳን የማያስችል መሆኑንም አስፍረዋል።

## ወርልድ ፒስ ፋውንዴሽን ይፋ ያደረገው የአፍሪካ ሐገራት ደረጃ

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሞሪሼ ዬስ | 15 | ጋምቢያ | 29 | ኒጀር | 43 | ኮንጎ (ብራዛቪል) |
| 2 | ሲሼልስ | 16 | ሴኔጋል | 30 | ማሊ | 44 | ጊኒ |
| 3 | ኬፐቨርዴ | 17 | ማዳካስጋር | 31 | ሞዛምቢክ | 45 | ዚምቧቤዌ |
| 4 | ቦትስዋና | 18 | ግብፅ | 32 | ጅቡቲ | 46 | አንጎላ |
| 5 | ቱኒዚያ | 19 | ቡርኬናፋሶ | 33 | ካሜሩን | 47 | ኤርትራ |
| 6 | ጋና | 20 | ታንዛኒያ | 34 | ቶጎ | 48 | ሴንትራል አፍሪካ ሪፐብሊክ |
| 7 | አልጄሪያ | 21 | ሊቢያ | 35 | ሴራሊዮን | 49 | ኮትዲቯር |
| 8 | ናምቢያ | 22 | ሞሪታኒያ | 36 | ጊቢቢሣው | 50 | ኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ |
| 9 | ደቡብ አፍሪካ | 23 | ሌሴቶ | 37 | ኢትዮጵያ | 51 | ቻድ |
| 10 | ሣኦቶሜ እና ፕንቼፔ | 24 | ዛምቢያ | 38 | ናይጄሪያ | 52 | ሱዳን |
| 11 | ጋቦን | 25 | ኮሞሮስ | 39 | ብሩንዲ | 53 | ሶማሊያ |
| 12 | ሞሮኮ | 26 | ሩዋንዳ | 40 | ላይቤሪያ | | |
| 13 | ቤኒን | 27 | ኬንያ | 41 | ኢኳቶሪያል ጊኒ | | |
| 14 | . ማላዊ | 28 | ኡጋንዳ | 42 | ስዋዚላንድ | | |

**በ2009 የተለቀቀው ሪፖርት እስከ 2007 ያለውን ብቻ የሚሸፍን ነው**

## በዋርልድ ፒስ ፋውንዴሽን ጥናት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ነጥብና ደረጃ

| | 2000 | 2000 | 2002 | 2002 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ነጥብ | በአፍሪካ ያገኙት ደረጃ | ነጥብ | በአፍሪካ ያገኙት ደረጃ | ነጥብ | በአፍሪካ ያገኙት ደረጃ | ነጥብ | በአፍሪካ ያገኙት ደረጃ | ነጥብ | በአፍሪካ ያገኙት ደረጃ |
| ጅቡቲ | 55.6 | 21 | 55.4 | 25 | 54.4 | 31 | 56.7 | 31 | 56.7 | 32 |
| ኤርትራ | 39.1 | 48 | 44.9 | 45 | 45.5 | 45 | 44.7 | 47 | 44.4 | 47 |
| ኢትዮጵያ | 44.5 | 44 | 50.9 | 36 | 52.7 | 34 | 51.4 | 37 | 51.1 | 37 |
| ኬንያ | 57.7 | 19 | 58.2 | 21 | 59.8 | 18 | 59.2 | 24 | 58.2 | 27 |
| ሶማሊያ | 21.9 | 53 | 20.9 | 53 | 22.0 | 53 | 18.4 | 53 | 16.3 | 53 |
| ሱዳን | 34.5 | 51 | 35.1 | 51 | 33.8 | 51 | 33.4 | 51 | 34.8 | 52 |
| ኡጋንዳ | 49.4 | 34 | 53.2 | 30 | 53.4 | 33 | 57.9 | 27 | 57.8 | 28 |

## የምሥራቅ አፍሪካ ሐገራት በየዘርፉ ያገኙት ነጥብ

| | ደህንነትና ፀጥታ | በአፍሪካ ያገኙት ደረጃ | የሕግ የበላይነት ግልፅነትና ሙስና | በአፍሪካ ያገኙት ደረጃ | ሕዝባዊ ተሳትፎ እና ሠብዓዊ መብት | በአፍሪካ ያገኙት ደረጃ | ቀጣይነት ያለው የኢኮሚ ዕድል | በአፍሪካ ያገኙት ደረጃ | ሰብዓዊ ልማት | በአፍሪካ ያገኙት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጅቡቲ | 94.4 | 17 | 45.0 | 37 | 48.9 | 35 | 37.2 | 23 | 57.9 | |
| ኤርትራ | 89.4 | 23 | 46.0 | 36 | 10.3 | 52 | 29.6 | 48 | 46.6 | 38 |
| ኢትዮጵያ | 80.3 | 34 | 49.2 | 33 | 38.1 | 42 | 36.2 | 28 | 51.8 | 29 |
| ኬንያ | 76.2 | 40 | 52.9 | 26 | 59.3 | 31 | 38.6 | 20 | 63.7 | 13 |
| ሶማሊያ | 33.3 | 53 | 5.6 | 53 | 4.9 | 53 | 3.2 | 53 | 34.4 | 50 |
| ሱዳን | 35.5 | 52 | 29.0 | 50 | 11.9 | 51 | 38.2 | 21 | 59.4 | 18 |
| ኡጋንዳ | 81.3 | 33 | 54.4 | 23 | 63.1 | 27 | 35.8 | 30 | 54.5 | 23 |

*ምን ማለት ነው?*

***1/ Safety & Security /ደህንነትና ፀጥታ/***

**Safety** የሚለው ከግድያ ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን መሠረት አድርጎ ከሚች ቁጥር ላይ የሚነሳ ሲሆን፣ **Security** የሚለው ደግሞ- ወታደራዊ ግጭትንና በወታደራዊ ግጭት የሞቱ ተዋጊዎችን እንዲሁም የሲቪላችን ሞት፣ የስደተኞችንና የጥገኝነት ጠያቂዎችን ቁጥር፣ በሐገር ውስጥ ከቦታ ቦታ የሚደረግ መፈናቀልን፣ ሕዝቡ ቀላል መሣሪያ ዎችን ለማግኘት ያለውን ምቹ ሁኔታ (acsess) መሠት ያደረገ ነው፡፡

***2/ Rule of law, Transparency and Corruption /የሕግ የበላይነት፣ ግልፅነት እና ሙስና/***

ዓለም አቀፍ የሠብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን መቀበልን፣ ዓለም አቀፍ ማዕቀብን፣ የንብረት መብትን፣ የፎርድ ቤ ት ነፃነትን፣ የፍርድ ቤቶችን የሥራ ብቃት፣ የሥራ ክርክር ጉዳዮችን ለመወሰን የሚወስደው ጊዜ እና በሕዝብ አገልግሎት ተቋማት ውስጥ የሚፈፀምን ሙስና መሠረት ያደረገ ነው፡፡

***3/ Participation and Human Rights /ሕዝባዊ ተሳትፎ እና ሰብዓዊ መብት/***

*ሀ/ ነፃ፣ ግልፅ እና የፉክክር ምርጫ*

- *ተቃዋሚዎች ለመንግስት አስፈፃሚ አካል በምርጫ የመሳተፍ ሁኔታ፣- ነፃና ግልፅ የሕግ አውጪ ምርጫ መኖር ፣ተቃዋሚዎች ለሕግ አውጭው አካል ምርጫ የሚያደርጉት ተሳትፎ*

*ለ/ - የአካል ደህንነት መብት፣- የሙያ ማህበራት ነፃነት፣ የፕሬስ ነፃነት፣ የሴቶች መብት*

***4/ Sustainable Economic Opportunity (ተቀጣይነት ያለው የኢኮሚ ዕድል)***

አጠቃላይ ሐገራዊ ምርት የነፍስ ወከፍ ድርሻ /GDP Per Capita/፣የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ግሽበት /**inflation**/፣ የመንግሥት የበጀት መትረፍ / መጉደል /**Surplus/ Deficits**/፣ የመንግሥት ተቋማት ታማኝነት፣ ለንግድ/ ኢንቨስትመንት ወዘተ ያለ ምቹ ሁኔታ፣ቢዝነስ ለመጀመር የሚፈጀው ጊዜ፣ለንግድ ያለ አመቺነት፣ የመንገዶች ሁኔታ፣ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅም፣ የቴሌፎን ደምበኞች ብዛት፣- የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ብዛት ወዘተ፤

***5/ Human development (ሰብዓዊ ልማት)***

ድህነትና ኢ-ዕኩልነት፣ በሐገሪቱ የድህነት መሥፈርት የድሆች ብዛት፣ በቀን ለአንድ ሠው 1.25 ዶላር እና ከዚያ በታች ገቢ የሚያገኙ ድሆች ብዛት

**6/**Health & sanitation /**ጤና እና ንፅህና አጠባበቅ**/ የሕፃናት ሞት፣ በምግብ እጥረትና ባልተመጣጠነ ምግብ ሣቢያ የሚከተል የጤና ችግር፣ የበሽታ መከላከያ ክትባቶችን የማግኘት ሁኔታ፣ በሽታዎች ያለ ተጋላጭነት፣ የጤና ባለሙያዎች ብዛት፣ የሐኪሞችና ነርሶች ብዛት ከሕዝብ ቁጥር አንፃር፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃ የማግኘት መጠን፣ ንፅህናቸው የተጠበቁ ቁሳቁሶችን የመጠቀም ሁኔታ፣

7/Education/**ትምህርት** ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ጎልማሶች ብዛት፣ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሴቶች ብዛት፣አንደኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቁ ብዛት፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቁ ብዛት፣ የወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች ብዛት በንፅፅር ፣የመምህራን ብዛት ከተማሪዎች ቁጥር አንፃር

የ**World Peace Foundation** ጥናት እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች መሠረት አድርጎ የወጣ መሆኑ በሪፖርቱ ተዘርዝሯል፤እነዚህ አጠቃላይ ሁኔታዎች ተገምግመውና እያንዳንዱ ነጥብ ተሰጥቶት፣ የነጥቡን ድምር መሠረት በማድረግ የሐገሮች የመልካም አስተዳደር ደረጃ ወጥቷል፤ይህ የዓለም ሠላም ፋውንዴሽን / **World Peace Foundation**/ ዓመታዊ ሪፖርት የሚጠናቀረው በዓለም ዝነኛ በሆነው በአሜሪካው ሐርቫርድ ዩኒቨርሲቲ አዋቂዎችና እና በአፍሪካ ሐገራት በሚገኙ ተመራማሪዎች ነው፤ የፋውንዳሽኑ ፕሬዚዳንት **Robert I, Rotberg** እና

Rachel m. Eisselquist የተመራማሪውን ቡድን የሚመሩ መሆኑን እዚህ ላይ በማስታወስ ቀደም ባለው ገፅ በጥቅል የተመለከትነውን ቀጥሎ በዝርዝር እንመለከታለን፤ ይበልጥ ሪፖርቱ ግልጽ ሆኖ የሚታየውና በደንብ የሚገባን በየዘርፉ የተገኘውን ነጥብ በአብዛኛው ደካማ ከሆኑት ጎረቤቶቻችን ጋር ስናነጻጽር ነው።

ዋርልድ ፒስ ፋውንዴሽን በዚህ የ2009 ሪፖርቱ በሕግ የበላይነት ሥር በጥቅል የተቀመጡትን በዝርዝር ነጥብ እየሠጠ ተመልክቷል፤ የፍሪደም ሀውስ /freedom house/ ጥናቶችን ጭምር ዋቢ በማድረግ ባጠናቀረው በዚህ ሪፖርቱ የፍርድ ቤቶችን ነፃነት በተመለከተ የምሥራቅ አፍሪካ ሐገሮች ሁሉም ዝቅተኛ ነጥብ ያገኙ ሲሆን፣ከኬንያ በቀር ሌሎች ያገኙት ነጥብ ከግማሽ በታች ነው፤ ኡጋንዳ ደግሞ ከቀሪዎቹ ትሻላለች።

## Judicial Independence & Efficiency of courts
## (የፍርድ ቤቶች/ዳኞች ነፃነትና-የሥራ ቅልጥፍናቸው/ብቃታቸው )

| | የፍርድ ቤቶች ነፃነት በመቶኛ (%) | የፍርድ ቤቶች የሥራ ቅልጥፍና/ብቃት በመቶኛ(%) |
|---|---|---|
| ጅቡቲ | 35.7 | 43.5 |
| ኤርትራ | 14.3 | - |
| ኢትዮጵያ | 28.6 | - (ነጥብ አልተሰጠም) |
| ኬንያ | 50 | 54.7 |
| ሶማሊያ | 0 | - |
| ሱዳን | 0 | 94.8 |
| ኡጋንዳ | 42.9 | 44.0 |

## የፍርድ ቤቶች ነፃነት ከ2000-2007

| | 2000 | 2000 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ያገኘት ነጥብ በመቶኛ | ደረጃ | ያገኘትነጥብ በመቶኛ | ደረጃ | ያገኘትነጥብ በመቶኛ | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 35.7 | 30 | 35.7 | 31 | 35.7 | 31 |
| ኤርትራ | 21.4 | 41 | 14.3 | 44 | 14.3 | 44 |
| ኢትዮጵያ | 35.7 | 30 | 28.6 | 35 | 28.6 | 35 |
| ኬንያ | 57.1 | 16 | 57.1 | 17 | 50 | 20 |
| ሶማሊያ | 21.9 | 41 | 0 | 50 | 0 | 50 |
| ሱዳን | 0 | 51 | 0 | 50 | 0 | 50 |
| ኡጋንዳ | 50 | 23 | 50 | 22 | 42.9 | 24 |

# ሙስና /Corruption/

| | 2000 | 2000 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 34.0 | 25 | 28.0 | 31 | 38.0 | 17 | 40.0 | 19 |
| ኤርትራ | 42.0 | 19 | 38.0 | 18 | 36.0 | 20 | 32.0 | 30 |
| ኢትዮጵያ | 44.0 | 17 | 28.0 | 31 | 28.0 | 34 | 32.0 | 30 |
| ኬንያ | 20.0 | 42 | 24.0 | 40 | 22.0 | 41 | 22.0 | 38 |
| ሱማሊያ | 22.0 | 39 | 22.0 | 47 | 8.0 | 53 | 0 | 53 |
| ሱዳን | 16.0 | 47 | 20.0 | 50 | 16.0 | 51 | 12.0 | 50 |
| ኡጋንዳ | 18.0 | 45 | 34.0 | 22 | 36.0 | 20 | 32.0 | 30 |

# Participation in Elections (የምርጫ ተሳትፎ )

| | ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ማካሄድ በመቶኛ (%) | | በምርጫ ጫቅት የተቃዋሚዎች ተሳትፎ በመቶኛ (%) | |
|---|---|---|---|---|
| | የአስፈፃሚ | የፓርላማ | የአስፈፃሚ | ፓርላማ |
| ጅቡቲ | 50 | 0 | 0 | 100 |
| ኤርትራ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ኢትዮጵያ | 0 | 0 | 100 | 100 |
| ኬንያ | 50 | 50 | 100 | 100 |
| ሶማሊያ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ሱዳን | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ኡጋንዳ | 50 | 50 | 100 | 100 |

## ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ (የአስፋፃሚዎች) free & fair Elections /executives/ 2000-2007

| | 2000 | 2000 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 50 | 7 | 50 | 9 | 50 | 10 | 50 | 9 |
| ኤርትራ | 0 | 27 | 0 | 29 | 0 | 33 | 0 | 35 |
| ኢትዮጵያ | 0 | 27 | 0 | 29 | 0 | 33 | 0 | 35 |
| ኬንያ | 50 | 7 | 50 | 9 | 50 | 10 | 50 | 9 |
| ሱማሊያ | 0 | 27 | 0 | 29 | 0 | 33 | 0 | 35 |
| ሱዳን | 0 | 27 | 0 | 29 | 0 | 33 | 0 | 35 |
| ኡጋንዳ | 50 | 7 | 50 | 9 | 50 | 10 | 50 | 9 |

**በ200 የመጨረሻው ደረጃ 27ኛ ሲሆን፣ በ2005-29ኛ፤ በ2006-33ኛ እንዲሁም በ2007-35ኛ የመጨረሻ ደረጃ ናቸው፤ከላይ የወጣው ሠንጠረዥ የአስፈፃሚ አካላትን ምርጫ የተመለከተ ሲሆን፣ በሕግ አውጭ /ፓርላማ ምርጫን በተመለከተም ኤርትራ፣ ኢትዮጵያ፣ ሱማሊያና ሱዳን በተመሳሳይ ዜሮ ነጥብ በማግኘት የመጨረሻው ደረጃ ላይ ሲሆኑ፣ ጅቡቲም፣ እዚህጋ ዝቅተኛውን ጎራ ስትቀላቀል፣ ኬንያና ኡጋንዳ የተሻለ ደረጃ አስመዝግበዋል፤ የአስፈፃሚ አካላት ምርጫ የሚባለው በዋናነት ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በሚካሄድባቸው ሐገራት ፕሬዚዳንቱን ለመምረጥ የሚካሄደውን ምርጫ የተመለከተ ነው፤ ከአፍሪካ ሐገሮች ፕሬዜዳንታዊ ምርጫ የማታደርግ ወይንም በጠ/ሚ/ር የምትመራ (*Parliamentary republic የምትከተል) ብቸኛ ሀገርኢትዩጵያ ነች።***

## የአካል ደህንነት ጥበቃ /ክብር መብት Respect for physical integrity Rights/

| | 2000 | 2000 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 75.0 | 11 | 62.5 | 16 | 75.0 | 5 | 75.0 | 7 |
| ኤርትራ | 75.0 | 11 | 25.0 | 42 | 25.0 | 42 | 25.0 | 44 |
| ኢትዮጵያ | 25.0 | 38 | 0 | 52 | 12.5 | 47 | 12.5 | 49 |
| ኬንያ | 25.00 | 38 | 37.5 | 32 | 37.5 | 34 | 37.5 | 35 |
| ሱማሊያ | 0 | 49 | 0 | 52 | 0 | 53 | 0 | 53 |
| ሱዳን | 0 | 49 | 12.5 | 51 | 12.5 | 47 | 12.5 | 49 |
| ኡጋንዳ | 25.0 | 38 | 25.0 | 42 | 12.5 | 47 | 37.5 | 35 |

## የሲቪል መብት ጥበቃ/ክብር Respect for civil Rights

ዜጎች በሐገራቸው ጉዳይ ላይ እኩል መብት አላቸው፤ ይህም ፆታን፣ ዘርን፣ እምነትን ወዘተ ልዩነት ሳያደርግ ለሁሉም እኩል ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ ስለመሆኑ እና የሙያ ማህበራት የመደራጀት መብትና ነፃነት መከበርን በተመለከተ ተቋሙ የሠጠው ነጥብና ደረጃ የሚከተለው ነው፡፡

| | 2000 | 2000 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 33.3 | 33 | 25.0 | 33 | 41.7 | 31 | 50.0 | 20 |
| ኤርትራ | 33.0 | 33 | 0 | 51 | 0 | 50 | 0 | 50 |
| ኢትዮጵያ | 41.7 | 29 | 50.0 | 23 | 41.7 | 31 | 16.7 | 44 |
| ኬንያ | 41.7 | 29 | 75.0 | 9 | 66.7 | 15 | 25.0 | 39 |
| ሶማሊያ | 0 | 49 | 0 | 51 | 0 | 50 | 0 | 50 |
| ሱዳን | 0 | 49 | 8.3 | 47 | 0 | 50 | 0 | 50 |
| ኡጋንዳ | 25.0 | 42 | 16.7 | 41 | 58.3 | 20 | 16.7 | 44 |

## የፕሬስ ነፃነት Press freedom

| | 2000 | 2000 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 76.4 | 38 | 71.2 | 35 | 74.8 | 36 | 59.0 | 40 |
| ኤርትራ | 28.4 | 52 | 13.7 | 52 | 15.8 | 52 | 0 | 52 |
| ኢትዮጵያ | 70.7 | 42 | 66.6 | 42 | 36.4 | 51 | 47.4 | 48 |
| ኬንያ | 82.4 | 26 | 77.6 | 31 | 77.3 | 34 | 83.3 | 17 |
| ሶማሊያ | 63.8 | 48 | 51.0 | 49 | 58.1 | 47 | 39.6 | 51 |
| ሱዳን | 72.1 | 41 | 64.8 | 43 | 61.0 | 44 | 54.0 | 43 |
| ኡጋንዳ | 89.5 | 10 | 87.4 | 18 | 77.7 | 33 | 79.4 | 25 |

## ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድል Sustainable Economic Opportu-

| | 2000 | 2000 | 2002 | 2002 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 34.0 | 18 | 35.9 | 17 | 36.9 | | 37.5 | 20 | 37.2 | 23 |
| ኤርትራ | 21.5 | 51 | 28.7 | 45 | 29.6 | 47 | 28.5 | 49 | 29.6 | 48 |
| ኢትዮጵያ | 32.1 | 27 | 30.5 | 41 | 35.6 | 21 | 35.8 | 26 | 36.2 | 28 |
| ኬንያ | 31.6 | 29 | 31.8 | 30 | 35.6 | 20 | 37.1 | 22 | 38.6 | 20 |
| ሶማሊያ | 1.6 | 53 | 1.4 | 53 | 3.1 | 53 | 3.2 | 53 | 3.2 | 53 |
| ሱዳን | 32.6 | 24 | 32.6 | 26 | 34.0 | 19 | 37.7 | 19 | 38.2 | 21 |
| ኡጋንዳ | 32.8 | 23 | 33.5 | 22 | 34.0 | 25 | 36.2 | 25 | 35.8 | 30 |

# የገንዘብ ተቋማት ተዓማኒነት/ታማኝነት Reliability of funancial institutions

ዋርልድ ፔሴ ፋውንዴሽን የዓለም አቀፉን የገንዘብ ተቋም መረጃ መሠረት በማድረግ ባወጣው ደረጃና በሰጠው ነጥብ፣ በ2007 ቦስትዋና ከአፍሪካ ቀዳሚውን ስፈራ ስትይዙ ናምቢያ በ2ኛ ደረጃ ላይ ስትገኝ፣ ደቡብ አፍሪካ ሶስተኛ ሆናለች፤ የምስራቅ አፍሪካ ሐገራትን ይመልከት፡፡

| | 2000 | 2000 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ | ነጥብ | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 81.3 | 16 | 86.3 | 11 | 85.7 | 16 | 86.9 | 14 |
| ኤርትራ | 84.1 | 14 | 82.2 | 18 | 84.2 | 17 | 83.2 | 20 |
| ኢትዮጵያ | 78.4 | 19 | 77.5 | 25 | 77.4 | 25 | 77.4 | 28 |
| ኬንያ | 87.3 | 10 | 88.3 | 9 | 88.5 | 10 | 87.8 | 10 |
| ሶማሊያ | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ሱዳን | 51.4 | 46 | 68.8 | 36 | 65.4 | 39 | 67.1 | 41 |
| ኡጋንዳ | 73.0 | 26 | 74.4 | 30 | 72.5 | 31 | 74.1 | 32 |

# መንገድ /Road

በአፍሪካ ሐገራት ያሉ መንገዶች ርዝመት በዚሁ በዋርልድ ፒሴ ፋውንዴሽን ሪፖርት ላይ የተዘረዘረ ሲሆን፣ ይህም ከየሐገራቱ የመስኩ ተቋም የተገኘውን መረጃ በአንድ በኩል፣ IRF የተባለ ተቋም ያወጣውን ደግሞ በማነፃፀሪያነት ያቀርባል፤ ሆኖም በሁለቱም መካከል ብዙም የጎላ ልዩነት ስለማይታይ ከየሐገራቱ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ የቀረበውንና ከየሀገራቱ ቆዳ ስፋት አንፃር ያለውን መንገድ ርዝመት በማነፃፀር ተቋሙ ያወጣውንም ደረጃ እንመለከታለን፡፡

***የምስራቅ አፍሪካ ሐገራት አጠቃላይ የመንገድ ርዝመት በኪሎ ሜትር***

| | 2000 አጠቃላይ የመንገድ ርዝመት በኪ.ሜትር | 2000 ደራጃ ከየሀገራቱ የቆዳ ስፋት አንፃር የሸፈነው ቦታ) | 2006 አጠቃላይ የመንገድ ርዝመት በኪ.ሜትር | 2006 ደራጃ (ከየሀገራቱ የቆዳ ስፋት አንፃር የሸፈነው ቦታ) |
|---|---|---|---|---|
| ጅቡቲ | 3,065 | 8 | 3,086 | 9 |
| ኤርትራ | 4,010 | 40 | - | 45 |
| ኢትዮጵያ | 31,554 | 51 | 39,477 | 51 |
| ኬንያ | - | - | 63,572 | 38 |
| ሶማሊያ | 22,100 | 31 | | 32 |
| ሱዳን | 11,900 | 49 | | 50 |
| ኡጋንዳ | - | - | 70,746 | 23 |

በመቶ ስኩዌር ኪሎ ሜትር የመሬት ክልል ውስጥ የኢትዮጵያ መንገድ ርዝመት በፈረንጆች 2000 ዓመተምህረት 0.38 በመቶ ሲሆን በ2006 0.50 በመቶ ደርሷል፤ የኤርትራ በ2000 0.87 ሲሆን፣ በ2006 እዚያው ላይ ይገኛል፤ ኬንያ አሁን 1.57 በመቶ ደርሳለች፡፡ ሲሼዬልስ እና ሞሪሽየስ 95.5 በመቶ እና 92.2 በመቶ ደርሰዋል፤ የኢህአዴግ መንግስት ከምርጫ 97 በኋላ መንገድ እየሰራ መሆኑ እርግጥ ቢሆንም፤በሀገሪቱ ሊሰራ ከሚገባው መንገድ አንድ በመቶ እንኳን አለመሰራቱን ከመረጃው መገንዘብ ይቻላል፤ከ 53ቱ የአፍሪካ ሀገራት የምንገኝበትም ደረጃ 2 ሀገራትን ብቻ በመቅደም 51ኛ ነው፡፡ ...ስለ ሀገሪቱ የቆዳ ስፋት እና አቅም ወዘተ በመጥቀስ መከራከሪያ ለሚያቀርቡ በሌላ ፅሑፍ በዝርዝር የምመለስበት ይሆናል፤ሆኖም አንድ ነገር ብቻ ጠቅሶ ለማለፍ የኢህአዴግ መንግስት በአንድ አመት ብቻ ከውጭ በእርዳታና በብድር የሚያገኘው ገንዘብ በአዲስ አበባ እስከዛሬ የሰራውን መንገድ (ቀለበት መንገዱን ጨምሮ) ሰርቶ ከግልገል ግቤ 2 የሚበልጥ የሀይል ማመንጫ ለመገንባት የሚበቃ ስለመሆኑ የኢህአዴግን መንግስት የገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት ማየት ይበቃል፡፡

## የኤሌክትሪክ ኃይል አቅም የነፍስ ወከፍ ድርሻ

| | 2002 | 2005 | 2006 | 2007 |
|---|---|---|---|---|
| | ደረጃ | ደረጃ | ደረጃ | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 15 | 13 | 13 | 13 |
| ኤርትራ | 37 | 31 | 31 | 31 |
| ኢትዮጵያ | 51 | 43 | 43 | 43 |
| ኬንያ | 29 | 28 | 29 | 29 |
| ሶማሊያ | 44 | 49 | 49 | 49 |
| ሱዳን | 35 | 33 | 33 | 33 |
| ኡጋንዳ | 43 | 44 | 44 | 44 |

በሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን ጥናትም ኢትዮጵያ በ2002ዓ.ም 45ኛ፣ በ2005 ዓ.ም 44ኛ እንዲሁም በ2006-በ40ኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧታል፤የሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን ጥናት ከሰሃራ በታች ባሉት 48 ሀገራት ላይ ብቻ የሚየተኩር መሆኑ ይታወቃል፡፡በሁለቱም ተቋማት ጥናት በአፍሪካ ውስጥ ካሉ ሀገራት ቢንስ 40 ዎቹ በሚያመነጩት የኤሌክትሪክ ሃይል የነፍስ ወከፍ ድርሻ ይበልጡናል፡፡ከዚህ የምንረዳው ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ሓይል ልትሸጥላቸው ነው በሚል ስማቸው የሚነሳው ጎረቤት ሀገሮች አሁን ባለው ደረጃ ከህዝባቸው ቁጥር አንፃር የሚያመነጩት ሃይል ከኢትዮጵያ በእጅጉ የተሻለ መሆኑን ነው፤ እርግጥ ነው ኢትዮጵያ ዕምቅ ሃይሉ እንዳላት ባለሙያዎች ያረጋገጡት ቢሆንም፣እምቅ ዕውቀት ያላቸው ልጆቿ ተገፍተው ሀገሪቱ ከየብሄረሰቡ በታማኝነት ለሚመለመሉ ጀማሪዎች መሞከሪያ መሆኗም ግልፅ ነው፡፡...

አንድ አብነት እዚህ ላይ ማንሳት ይቻላል፤ኢሕአዴግ አደርገዋለሁ ባለው ሽግሽግ ስልጣናቸውን ከሚለቁ ባለስልጣናት አንዱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሥዩም መስፍን ናቸው፤በነገራችን ላይ አቶ ስዩም

እስካሁን ባለው ሪከርድ በአለም ላይ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ስልጣን ላይ ረጅም ዘመን ካስቀጠሩ በሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፤... አቶ ስዩምን ለማንሳት ኢህአዴግ መወሰኑን ተከትሎ ርሳቸውን ማን ይተካቸዋል የሚለው አነጋጋሪ ሆኖ መገኘቱ 80 ሚሊዮን ሕዝብ ያለባትና ባዕዳንን የሚያገለግሉ በርካታ ሺህዎች ስለበቀሉባት ኢትዮጵያ ሳይሆን ከ 10 ሺ ብዙም ፈቀቅ ያላለ ሕዝብ ስላላት ቱቫሉ የሚያወሩ እስኪመስለን ተገርመናል፤ለሥርአቱ ባለስልጣናት ቅርብ የሆነ ጋዜጣ በሹክሹክታ እንደዳስነበበን ከሆነ ብአዴንና ኦህዴድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱ ቦታ ይገባናል የሚል ፉክክር ውስጥ ቢገቡም ከእነሱ ብቃት ያለው ሰው ባለመኖሩ ትኩረቱ በህወሀት ሰዎች ላይ ሆኗል።በታላላቅ አለም አቀፍ ተቋማት ታላላቅ ቦታ የያዙ *(ለምሳሌ የአለም ቀይ መስቀል ዋና ፀኃፊ አቶ በቀለ ገለታ፣የዩኔስኮ መክትል ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው እንግዳ)* ከኦሮሞ፣ከአማራ ብሄረሰብ የተወለዱ በርካታ ምሁራን ለባዕአዳን በተረፉበት የአማራ እና የኦሮሞ ወኪል ነን በሚሉት ብአዴንና ኦህዴድ ውስጥ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት የሚበቃ ሰው መጥፋቱ ለምን የሚል ጥያቄ ማንሳት ያለበት ከማንም በላይ ሕወሃት ነው፤ (በርግጥ ችግሩ የብቃት ብቻ እንዳልሆነም ይታወቃል) ...የቁልቁል ጉዟችን የተጀመረው ዛሬ በዚህ ዘመን ባይሆንም የአለም ሀገራት ከገቢያቸው ቀንሰው በአመት ከቢሊዮን ዶላር በላይ እየረዱንና እያበደሩን የአለምም የአፍሪካም ጭራ መሆናችን፣ከኢህአዴግ ሥልጣን በኋላ በተስፋፋው የሞባልና የኢንተርኔት ቴክኖሎጂ የአለም ጭራ ሆነን ከመንግስት አልባዋ ሶማሊያ ጭምር ማነሳችን ህሊና ላለው የሚያም ነው።

## የቴሌፎን ተጠቃሚዎች (በላይዞታዎች) ብዛት   Telephone Subscribers

ዓለም አቀፉን የቴሌኮሚኒኬሽን ማኅበር /international telecommunication union/ መረጃን ዋቢ በማድረግ ዋርልድ ፒስ ፋውንዴሽን ያጠናቀረው ዘገባ የመደበኛ ስልክንና ተንቀሳቃሽ /ሞባይልን ያጠቃልላል። እንዲሁም የኢንተርኔት ተጠቃሚዎችን ብዛት አስፍሯል፤እዚህ ላይ በአፍሪካ ሐገራት ከ100 /መቶ/ ሰው ውስጥ ምን ያህሉ የመደበኛ ሥልክ ተጠቃሚ እንደሆነና ሀገራቱ ያላቸውን ደረጃ በዝርዝር አቅርቧል።

### *ከእያንዳንዱ መቶ ሰው የስልክ ባለቤት ብዛትና ደረጃ*

| | 2000 | 2000 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | ደረጃ | ብዛት | ደረጃ | ብዛት | ደረጃ | ብዛት | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 1.1 | 27 | 5.6 | 36 | 5.6 | 42 | 5.6 | 46 |
| ኤርትራ | 0.7 | 34 | 1.4 | 51 | 1.8 | 51 | 2.1 | 52 |
| ኢትዮጵያ | 0.3 | 49 | 1.1 | 52 | 1.7 | 52 | 2.2 | 50 |
| ኬንያ | 1.1 | 28 | 11.4 | 22 | 17.3 | 20 | 25.6 | 17 |
| ሶማሊያ | 1.1 | 26 | 5.9 | 34 | 6.3 | 39 | 6.6 | 44 |
| ሱዳን | 0.9 | 32 | 5.1 | 37 | 10.9 | 31 | 17.6 | 27 |
| ኡጋንዳ | 0.6 | 38 | 4.0 | 40 | 5.9 | 41 | 11.8 | 37 |

ከዚህ አሃዝ መረዳት የሚቻለው በኬንያ ከአራት ሰው አንዱ ወይንም እያንዳንዱ ቤተሰብ የስልክ ተጠቃሚ መሆኑን ሲያሳይ፣ በኢትዮጵያ ከ50 ሰዎች ውስጥ የስልክ ተጠቃሚው አንድ ብቻ መሆኑን ያስረዳል፡ በመንግስት አልባዋ ሶማሊያ ከ14 ሰዎች አንዱ፣ በአፍሪካ ቀዳሚውን ስፍራ በያዘችው ሲሺልስ ከእያንዳንዱ መቶ ሰው ሁሉም የስልክ ተጠቃሚ /ባለቤት/ ስለመሆኑ መረጃው ያስ ረዳል፤ ሞሪሽየስ እና ደቡብ አፍሪካ በ84.6 እና በ79.4 ይከተላሉ፤የሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽንን ሪፖርት በንጽጽር ስንመለከት

ኢትዮጵያ በ2000 ዓ.ም 44ኛ ፣በ2002 ዓ.ም 45ኛ፣ በ2005 48ኛ እንዲሁም በ2007 ዓ.ም 48ኛ መሆኗ_ተመልክቷል፡፡በሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽንን ሪፖርት የተካተቱት ከሰሐራ በታች ያሉት 48ቱ የአፍሪካ ሐገሮች ብቻ በመሆኑ ፣ 48ኛ የመጨረሻውን ደረጃ ያሳያል፡፡ በሞባይል ቴሌፎን በኩልም ያለነው ከአፍሪካም ዓለም ግርጌ ነው፤በ the ICT development index የ2009 ሪፖርት መሰረት በኢትዮጵያ የሞባይል ቴሌፎን ተጠቃሚው ከ2 በመቶ በታች 1.5% ሲሆን፣ከኢትዮጵያ ጋር በተመሳሰሳይ ወቅት አገልግሎቱን የጀመረችው ኬንያ እጅግ ረጅም ርቀት ተጉዛ 30.2 % ስትደርስ ሱዳን 21% ደርሳለች፤ኢሕአዴግ እንደትልቅ ስኬት በሚያወራው የሞባይል ቴሌፎን የተበለጥነው በእነ ኬንያ ብቻ ሣይሆን፣በኤርትራና በመንግስት አልባዋ ሶማሊያ ጭምር ነው፡፡

## I የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ብዛት ከእያንዳንዱ 100 ነዋሪዎች ውሥጥ internet Usage Per 100 inhabitants

| | 2000 | 2000 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተጠቃሚ ብዛት | ደረጃ | የተጠቃሚ ብዛት | ደረጃ | የተጠቃሚ ብዛት | ደረጃ | የተጠቃሚ ብዛት | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 0.5 | 27 | 3.2 | 32 | 3.5 | 34 | 3.5 | 37 |
| ኤርትራ | 0.3 | 33 | 4.6 | 26 | 5.6 | 27 | 6.5 | 30 |
| ኢትዮጵያ | 0.0 | 51 | 0.5 | 50 | 0.8 | 48 | 0.9 | 51 |
| ኬንያ | 0.8 | 18 | 8.1 | 21 | 19.6 | 10 | 20.7 | 12 |
| ሶማሊያ | 0.5 | 25 | 2.8 | 35 | 2.8 | 36 | 2.9 | 38 |
| ሱዳን | 0.1 | 49 | 3.3 | 30 | 21.1 | 8 | 22.5 | 9 |
| ኡጋንዳ | 0.4 | 31 | 4.5 | 27 | 6.6 | 26 | 9.5 | 24 |

ከዝርዝሩ ማየት እንደሚቻለው ኢትዮጵያ በኢንተርኔት ተጠቃሚነት ከአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ከምስራቅ አፍሪካም ዝቅተኛ፣ ከመንግስት አልባዋ ሶማሊያም እጅግ ያነሰች ሆና ተመዝግባለች፤ዓለም ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል መንግስታዊ መዋቅር ጉዞዋን ባፋጠነችበት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ትናንት ሀገር ሆና ከቆመችው ኤርትራ ለምን እናንሳለን? መንግስት አልባ ሆና 19 አመታት ያስቆጠረችው ሶማሊያ ወደ ሶስት እጥፍ እንዴት ቀደመችን ብሎ ከመቆጨትና ይበልጥ ከመትጋት ይልቅ አንድ ከመቶ የማይሞላው የኢንቴርኔት ተጠቃሚ ከመረጃ መረብ ውስጥ የፈቀደውን እንዳያነብ፣እነርሱ የፈለጉትን ብቻ እንዲከታተል የሀገሪቱ ገንዘብ ለድረ ገፆች አፈናም እየዋለ ይገኛል፤በዚህ በአፈናው መንገድ በርግጥ እየገሰገስን ነው፤በቻይና ቴክኖሎጂ ከቻይናና ከሰሜን ኮርያ ጋር እየተወዳደርን በመሆናችን ጨርሶ ከመረሳት በክፉም ቢሆን መወሳት ተሽሎ ይሆን ? የኢሕአዴግ መንግስት ሁሉን ነገር ከሩቅ ምስራቅ የሚያማትርበት ልክፍት ማርከሻው ካልተገኘ ስለዚህች ሀገር ብሩህ ዘመን ማሰብ ያስቸግራል፤መረሳት የሌለበት ግን ቻይና በአፈናው ብቻ ሳይሆን ኢንቴርኔትን ጨምሮ በጠቃሚ ቴክኖሎጂ እየገሰገሰች መሆኗ ነው፤የቅርብ ግዜ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከ300.000.000(ሶስት መቶ ሚሊዮን) በላይ ወይንም ከሀገሪቱ ሕዝብ ከ1/4ኛ (25%) በላይ የኢንተርኔት ተጠቃሚ ነው፤በፖለቲካውም መስክ በኮሚኒስት ፓርቲ ውስጥ የውሥጥ ዲሞክራሲ በመኖሩ የሀገሪቱም ሆነ የፓርቲው መሪዎች ሥልጣንን በርስትነት አልያዙም፤ዛሬ አቶ መለስን ጨምሮ በአለማችን ረዥም ዘመን ስልጣን ላይ ከቆዩ 20 መሪዎች ውሥጥ የቻይና መሪ አልተመዘገበም፡፡...የቻይናን ሞዴል እከተላለሁ የሚለው የኢህአዴግ መንግስት መጥፎ መጥፎውን ሣይሆን ጠቃሚውን ቢማርልን ለሁላችንም በበጀን ነበር፤በሌላም በኩል የቻይና ሕዝብ የባህልም ሆነ የቋንቋ ወጥነት የሚታይበት 92 በመቶ የ«ሀን» ብሄረሰብ በመሆኑ ይህ በራሱ የቻይናን ሞዴል ለመከተል አሉታዊ ሁኔታ ሊኖረው ስለሚችልም መፈተሽ ይገባዋል፡፡

# ሰብዓዊ ልማት Human development

## በየሀገራቱ ያሉ ሀኪሞች(ዶክተሮች) ብዛት -ለአንድ ሺህ ሰው የሚደርሰው በመቶኛ

| | 2000 | 2000 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛትበ % | ደረጃ | ብዛት በ % | ደረጃ | ብዛት በ % | ደረጃ | ብዛት በ % | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 6.7 | 20 | 6.7 | 20 | 6.7 | 20 | 6.7 | 20 |
| ኤርትራ | 1.2 | 38 | 1.2 | 38 | 1.2 | 38 | 1.2 | 38 |
| ኢትዮጵያ | 0.4 | 46 | 0.4 | 46 | 0.4 | 46 | 0.4 | 46 |
| ኬንያ | 4.9 | 25 | 4.9 | 25 | 4.9 | 25 | 4.9 | 25 |
| ሶማሊያ | 0.8 | 42 | 0.8 | 42 | 0.8 | 42 | 0.8 | 42 |
| ሱዳን | 8.3 | 17 | 8.3 | 17 | 8.3 | 17 | 8.3 | 17 |
| ኡጋንዳ | 2.5 | 33 | 2.5 | 33 | 2.5 | 33 | 2.5 | 33 |

## ከየሀገራቱ ሕዝብ ንፁህ ውሃ የሚያገኘው በመቶኛ

| | 2000 | 2000 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብ ዛ ት በመቶኛ | ደረጃ | ብ ዛ ት በመቶኛ | ደረጃ | ብ ዛ ት በመቶኛ | ደረጃ | ብ ዛ ት በመቶኛ | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 77.9 | 11 | 89.6 | 7 | 89.6 | 7 | 89.6 | 7 |
| ኤርትራ | 40.3 | 38 | 48.1 | 34 | 48.1 | 34 | 48.1 | 34 |
| ኢትዮጵያ | 7.8 | 52 | 24.7 | 50 | 24.7 | 50 | 24.7 | 50 |
| ኬንያ | 38.4 | 41 | 44.2 | 40 | 44.2 | 40 | 44.2 | 40 |
| ሶማሊያ | - | 53 | 7.8 | 53 | 7.8 | 53 | 7.8 | 53 |
| ሱዳን | 59.7 | 24 | 61.0 | 26 | 61.0 | 26 | 61.0 | 26 |
| ኡጋንዳ | 42.4 | 35 | 53.2 | 32 | 53.2 | 32 | 53.2 | 32 |

*ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ሩብ ያህሉ እንኳን ንፁህ ውሃ እንደማየገኝ ጥናቱ ያረጋግጣል፤ መንግስት አልባዋን ሶማልያን በማስከተል በዚህም የአፍሪካ ጭራ ነን፤በሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን ሪፖርትም ኢትዮጵያ መጨረሻ ላይ ተቀምጣለች፤በዚህም ሆነ በሁሉም ሠንጠረዥ ላይ (በገጽ 18 ካለው በቀር) «ደረጃ » በሚል የተቀመጠው የተጠቀሱት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት በአፍሪካ ውሥጥ ያላቸውን ቦታ የሚያሳይ ነው፡፡*

# ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ጎልማሶች Adult Literacy

| | 2000 | 2000 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብ ዛ ት በመቶኛ | ደረጃ | ብ ዛ ት በመቶኛ | ደረጃ | ብ ዛ ት በመቶኛ | ደረጃ | ብ ዛ ት በመቶኛ | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 71.2 | 19 | 71.2 | 25 | 71.2 | 25 | 71.2 | 25 |
| ኤርትራ | 47.4 | 35 | 63.1 | 32 | 63.1 | 32 | 63.1 | 32 |
| ኢትዮጵያ | 25.2 | 45 | 25.2 | 46 | 25.2 | 47 | 25.2 | 47 |
| ኬንያ | 75.6 | 16 | 75.6 | 17 | 75.6 | 18 | 75.6 | 18 |
| ሶማሊያ | - | 53 | - | 53 | - | 53 | - | 53 |
| ሱዳን | 58.6 | 30 | 58.6 | 33 | 58.6 | 33 | 58.6 | 33 |
| ኡጋንዳ | 68.3 | 23 | 75.6 | 17 | 75.6 | 18 | 75.6 | 18 |

*መሐይምነትን ሙሉ በሙሉ ከሐገርዋ በማስወገድ ቀዳማዊ አፍሪካዊት ሐገር በሁሉም የስኬትን አክሊል እየደፋች ያለችው ሲሺልስ ስትሆን፣ ዚምቧቤ ደግሞ 99.2 በመቶ ከመሐይምነት ነፃ በማውጣት ትከተላለች፤ ደቡብ አፍሪካ 94.9 በመቶ ከመሐይምነት ነፃ በማውጣት 3ኛውን ደረጃ አስመዝግባለች።*

## *የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ያጠናቀቁ ታዳጊዎች ብዛት እና የሐገራቱ ደረጃ*

| | 2000 | 2000 | 2005 | 2005 | 2006 | 2006 | 2007 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብ ዛ ት በመቶኛ | ደረጃ | ብ ዛ ት በመቶኛ | ደረጃ | ብ ዛ ት በመቶኛ | ደረጃ | ብ ዛ ት በመቶኛ | ደረጃ |
| ጅቡቲ | 14.2 | 39 | 18.0 | 44 | 23.1 | 45 | 23.1 | 46 |
| ኤርትራ | 24.2 | 34 | 42.3 | 32 | 39.1 | 36 | 36.1 | 39 |
| ኢትዮጵያ | 6.5 | 45 | 30.1 | 40 | 34.9 | 40 | 36.0 | 41 |
| ኬንያ | 88.1 | 7 | 91.2 | 7 | 91.2 | 5 | 91.2 | 7 |
| ሶማሊያ | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ሱዳን | 25.5 | 33 | 36.7 | 35 | 36.7 | 39 | 40.4 | 36 |
| ኡጋንዳ | 49.0 | 21 | 45.7 | 30 | 45.7 | 31 | 45.7 | 33 |

**የዎርልድ ፒስ ፋውንዴሽን ጥናትን እዚህ ላይ ገተን ከሌሎች አለም አቀፍ ጥናቶች ጥቂት ማነጻፀርያዎችን በማየት ዘገባውን እናጠቃልላለን።**

# ሌሎች ጥናቶችስ ምን ይላሉ?

## Bertelsmann transformation index , Democracy index

በርትልስማን(?) ስቲፈንግ (Bertelsmann Stiftung) የተባለው እና መቀመጫውን ጀርመን ያደረገው ተ ቋም በዚሁ ሐገር ሙኒክ ከተማ ከሚገኘው ሴንተር ፎር አፕላይድ ፖሊሲ ሪሰርች (Center for applied policy research) ተቋም ጋር ያደረገውን ጥናት ውጤት በቅርብ ወራት ይፋ አድርጓል፤ በዚህ ባለ 60 ገፅ በርትልስማን ትራንስፎርሜሽን ኢንዴክስ (Bertelsmann transformation index ) በፖለቲካዊና ኢኮሚያዊ እንዲሁም በማኔጅመንት የዓለም ሀገራትን አወዳድሮ ደረጃ ሰጥቷል፤በተቋሙ የ2008 ሪፖርት ኢትዮጵያ ከ10 ነጥብ 3.96 በማግኘት በአንድ መቶ ሐገሮች ተቀድማ 101ኛ ደረጃ ይዛለች፤በጥናቱ የተካተቱት 126 ሀገሮች ናቸው። ይህ ተቋም በፖለቲካና ኢኮኖሚ ይዞታ እንዲሁም በማነጅመንት ብቃት ላይ አተኩሮ ጥናቱን ሲያካሂድ የፖለቲካ ተሳትፎ፣ የሕግ የበላይነት፣ የገንዘብና የዋጋ መረጋጋት ወዘተ ለጥቅል ውጤቱ ዝርዝር መነሻ ነጥቦችን ይዘዋል።ተቋሙ ለኢትጵያ የሰጠውን ነጥብ፣ ከጎረቤት ኬንያና ኤርትራ ጋር በማነፃፀር ሰንጠረዡን ይመልከቱ።

| | ኢትዮጵያ (ከ10 ያገኘችው ነጥብ ) | ኬ ን ያ (ከ10 ያገኘችው ነጥብ ) | ኤርትራ ( ከ 1 0 ያ ገ ኘ ች ው ነጥብ ) |
|---|---|---|---|
| ዲሞክራሲያዊነት | 4.13 | 7.0 | 2.60 |
| የፖስቲካ ተሳትፎ | 3.0 | 8.0 | 1.3 |
| የሕግ የበላይነት | 3.5 | 6 | 2 |
| የዲሞክራሲ ተቅማት መ ፅ ና ት / መ ር ጋ ት (Stability of democracy institutions) | 2.0 | 7.0 | 1.0 |
| ፖለቲካዊና ማኅበራዊ መስተጋበር | 4.7 | 6.5 | 2.0 |

በኢኮኖሚና ማኔጅመንት ላይም በተ መሳሳይ ዝርዝር ጉዳዮች ተነስተው ነጥብ ተ ሰ ጥ ጥ ቷ ቸ ዋ ል ፤ በ B e r t e l s m a n n transformation index በፖለቲካና ኢኮኖሚ transformation (ሽግግር) በ2008 101ኛ የወጣችው ኢትዮጵያ ከቀደመው የተቋሙ የ2006 ጥናት ጋር ሲነፃፀር ደረጃዋ ዝቅ ያለ ሆኖ ተገኝቷል፤ በ2006 92ኛ ደረጃ ላይ ነበ ረች፤ በማኔጅመንት ደግሞ በ2008 91ኛ የወጣችው ኢትዮጵያ በ2006 ም በዚህ መስክ በተሻለ ደረጃ 83 ላይ ነበረች፤ በፖለቲካና ኢኮኖሚ ሽግግር በ2008 አንደኝነቱን የያዘችው ቼክ ሪፐብሊክ ስትሆን፣ ስሎቫኒያና ኦስትሪያ ይከተላሉ፣ በማኔጅመንት ደግሞ ቺሊ ስትቀድም ኦስትሪያና አፍሪካዊቷ ቦትስዋና 2ኛና 3ኛ ደረጃ ይዘዋል።በሌላም በኩል የዘ ኢኮኖሚስት ኢንተሊጀንስ ዩኒት (The Economist intelligence unit ) የ2008 ዳታዎችን መሰረት አድርጎ ባወጣው የዲሞክራሲ ያዊነት ደረጃ (Democracy index 2008) በጥናቱ ከተካተቱ ሀገሮች ኢትዮጵያ 105 ኛ ነች፤የምርጫ ሂደት እና ብዙሃንነት፣ መንግስት ተግባሩን የማከናወን ሁኔታ/አቅም /functioning of government/ ፤ የፖለቲካ ተሳትፎ፣ የፖለቲካ ባህል፣ ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት እና በነጻነት የመደራጀት መብት ... እነዚህን መሠረት በማድረግ ተቋሙ አወዳድሮ በሰጠው ነጥብ ስዊዲን፣ ኖርዌይ እና አይስላንድ 9.88፣ 9.68 እና 9.65 ከ10 በማግኘት ከአንድ እስከ ሶስተኛ ያለውን ደጃ ሲይዙ፣ ኢትዮጵያ በአጠቃላይ 4.52 ነጥብ በማግኘት የ105ኛ ደረጃ ላይ ተገናለች፤በምርጫ ሂደትና በብዙሃንነት 3.0፣ መንግስት ተግባሩን የመወጣት አቅም/ብቃት 3.93፣ የፖለቲካ ተ ሳትፎ 5.0፣ የፖለቲካ ባህል 6.25፣ ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት እና በነጻነት የመደራጀት መብት 4.41 አግኝታለች።


# Global Peace index

በዓለማችን ሐገራት ያለውን የፀጥታ ሁኔታ የሚገመግመውና ዓመታዊ ሪፖርት የሚለቀው ኢንስቲቲዮት ፎር ኤኮኖሚክስ ኤንድ ፒስ (institute for Economics & Peace) ከኢኮኖሚስት ኢንተሊጀንስ ዩኒት (Economist intelligence unit) እና ከፒስ ኢንስቲቲዩት (Peace institute) ጋር በተመባበር ያካሄደውን ጥናት የ2009 ሪፖርቱን ይፋ አድርጓል:: በዚህም ከ144 አገራት ኒውዝላንድን ፊት በማስቀደም ዴንማርክንና ፎርዌይን በ2ኛና 3ኛ ደረጃ ላይ በማስቀመጥ በአጠቃላይ ሰላም የሰፈነባቸው በማለት 29 ሐገራትን በቅደም ተከተል ሰያስቀምጥ፤ ሰላም የራቃቸው በማለት ደግሞ ሌሎች 29 ሐገራትን ከመጨረሻው አሰልፏቸዋል፤ ግርጌ ላይ ከ116ኛ እስከ 144ኛ ካስቀመጣቸው ሀገራት አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ በ128ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፤ ሱዳንና ሶማሊያም ከኢትዮጵያ በታች በዚሁ ዝርዝር ውስጥ ተካተዋል:: ኡጋንዳና ኬንያ ከዚህ ሰላም ከራቀቸው ዝርዝር ውስጥ አልገቡም:: አርትራን ደግሞ ጥናቱ አልጨመረም፤ በጥናቱ ከተካተቱት 31 የአፍሪካ ሐገሮች ኢትዮጵያ 24ኛ ነች፤የበለጠችው 7 ሀገራትን ብቻ ነው:: በ2007 በ121 ሐገሮች መካከል በተሰጠው ደረጃ ኢትዮጵያ 19 ሐገራትን ብቻ በማስከተል 102ኛ ነበረች፤ በ2008 ደግሞ ከ140 ሐገሮች 120ኛ ደረጃ ይዛለች::

ተቋሙ በሐገራት መካከል ያለውን የፀጥታ ሁኔታ ገምግሞ ደረጃ ለማውጣት የውጭና የውስጥ ግጭት መኖሩ ብቻውን የሁሉ ነገር መደምደሚያ አይደለም፤ በሐገራቱ ያሉ የፀጥታ ኃይሎችና የፖሊሶች ቁጥር ከነዋሪው ሕዝብ አንፃር፣ በሐገሪቱ የተመዘገቡ የፍስ ግድያ ወንጀሎች ብዛት፣ የእስረኞች ብዛት፣ የዓመፅ ተቃውሞዎች እና የዓመጽ መኖር አዝማሚያ፣ በኃይል የተደገፈ የተራጀ ወንጀል፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የሰብአዊ መብት መጣስ፣ ከጎረቤት ሐገራት ጋር ያለ ግንኙነት ወዘተ በጥናቱ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፤ሁሉም የየራሳቸው ነጥብ አላቸው::

# The failed states index

በዓለም ሐገራት ያሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮሚያዊና ማኅበራዊ እውነታዎትን በመተንተን የየሐገራቱን መንግስት ሕልውና የሚፈትሸው ዘ ፈንድ ፍር ፒስ /The fund for peace/ ከአሜሪካው ቲንክ ታንክ ( united states think-thank)እና ከፎሪየን ፖሊሲ (foreign policy) መፅሄት ጋር ከ 2005 ጀምሮ ላለፉት 5 አመታት በወጉ ያልቆሙ ወይንም አደጋ ላይ የሚገኙ /failed States/ በሚል በተከታታይ ሪፖርቶቹ ከዘረዘራቸው ሐገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ነች፤ሆኖም ከዋናዎቹ 20 ዎቹ ውስጥ መግባት የጀመረችው ከ2007 ጀምሮ ነው፤ ተቋሙ




በማኅበራዊ ፤በኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲዊ ጉዳዮች በአጠቃላይ 12 ነጥቦችን መሠረት አድርጎ በሚያደርገው ጥናት በሚከተሉት ላይ ያተኩራል፤ የሕዝብ ቁጥር አለቅጥ መጨመር፣ ከፍተኛ የስደተኞች ቁጥር፣ የኢኮኖሚ ማቆልቆል፣ ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚ ልማት፣ ሕዝብ ለመንግስት እውቅና መንፈግ፣ የደህንነት (ፀጥታ) እንቅስቃሴዎች፣ በመንግስት ውስጥ ሌላ መንግስት ወይንም ስውር መንግስት መኖር ፣የሌላ ሀገር መንግስት ወይንም የሌላ ሐገር ፖለቲከኞች ጣልቃ ገብነት፣ መንግስት ግዛቱን በተገቢው የመቆጣጠር አቅም ወዘተ.. የጥናቱ ዋነኛ

ግብአቶች ናቸው፤በዚህም መነሻነት በአደጋ ላይ የሚገኙ መንግስታት /failed states/ ደረጃ ከዓለም በቋፍ ላይ በመገኘት ዘንድሮም፣አምናም ካቻምናም ቀዳሚነቱን ሥፍራ የያዘችው ሶማሊያ ስትሆን፣ ሱደን በሁሉም ሪፖርቶች ከመጀመሪያዎቹ አምስት ውስጥ ትገኛለች፤ ኬንያ አምና እና ዘንድሮ የመጀመሪያዎቹ 20ዎቹ ውሥጥ ገብታለች፤ ኢትዮጵያ በ2007 18ኛ፣በ2008 16ኛ ደረጃ ላይ ነበረች፤ ከምስራቅ አፍሪካ ሐገራት ከዚህ አደጋ ቀጠና በመራቅ በ2009 ደረጃዋ 36ኛ ላይ የተመዘገበችው ኤርትራ ነች፤ በ2010 በተደረገው ጥናት ኢትዮጵያ 17ኛ ደረጃ ላይ ስትገኝ፣ሶማሊያ 1ኛ፣ሱዳን 3ኛ፣ኬኒያ 13ኛ፣ኡጋንዳ 21ኛ ሆነዋል፤ኤርትራ 30ኛውን ደረጃ በመያዝ ከምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የተሸለች ሆና ተመዝግባለች፤ሆኖም ከአደጋ ቀጠናው አልወጣችም፡፡ኖርዌይ፣ፊንላንድ፣ስዊድን እንደቅደም ተከተላቸው ከ1 እስከ 3ኛ ያለውን ደረጃ በመያዝ የአለም የሰለም ቁንጮ ሆነው ተመዝግበዋል፡፡

## ሰብዐዊ ልማት /human developent/

የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም የ2007ትን መረጃ መሰረት አድርጎ ይፋ ባደረገው ሪፖርት ኢትዮጵያ በሰብአዊ ልማት ከመቶ ሰማንያ ሁለት ሀገሮች 171ኛ ነች፤ የምትበልጠው 11 ሐገራትን ብቻ ነው፤የድህነት ደረጃን በበሚሳየው ሂውማን ፖቨርቲ ኢንዴክስ (**human poverty index) በመቶ ሰላሳ አምስት ሀገሮች ላይ በተካሄደ ጥናት ኢትዮጵያ በ135ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፤ከኢትዮጵያ በታች የተመዘገቡት አምስት ሀገሮች ብቻ ናቸው፡፡** ....በሁሉም መስክ የዓለም ጭራ ነን፤ ሀገራዊ ቅናት ይዞኝ ወደ ፊት የሚያመጣንን ጥናት ለማግኘት ሥቆፍር የሚመጣው ሁሉ «ዓሳ ጎርጓሪ ...» የሚለውን ብሂል የሚያስታውስ ውድቀት ብቻ ነው፤ገንዘብ ላለው በአለም ላይ ለኑሮ አዲስ አበባ ርካሽ ከተማ መሆኗን ግን አንብቤያለሁ፤ ... ዕርግጥ ነው እንደ ስኬት ከታየ ኢትዮጵያ በዓለም ላይ በቀዳሚዎቹ ሰፈር የተመዘገበችው በሕዝብ ቁጥር ብዛቷ ነው፤ኢትዮጵያ ዛሬ በዓለም ላይ በሕዝብ ቁጥር ብዛት ከዓለም 15ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፤ጥናቶች እንደሚያሳዩት የዛሬ 40 ዓመት በ2050 ደረጃዋን በማሻሻል በ174 ሚሊዮን ሕዝብ ከዓለም 9ኛ ደረጃ ላይ ትደርሳለች:: ከአፍሪካ ከናይጄሪያ ቀጥሎ ሁለተኛ ትሆናለች ማለት ነው፡፡... በተረፈ የዜጎቿ ኑሮ እንደሚመሰክረው፣ነባራዊውን እውነታ መዝግበውና ተንትነው፤ ከዓለም ሀገራት አመሳክረው ደረጃ የሚያወጡ ተቋማትም እንዳረጋገጡት በፖለቲካውም፣በኤኮኖሚውም፣በማህበራዊውም መስክ ወድቀናል፤ ዘወትር በሬዲዮና በቴሌቪዥን የሚለፈፈውን፣ በመንግስታዊ ጋዜጦች የሚፃፈውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን በውኑ በሕልሙም እያየው አይመስለኝም፤ተስፋ የራቀው ሕዝብ ቅዠት እንጂ ህልም ያያል እንዴ?... በአጭሩና በጥቅሉ ስለኢኮኖሚ እድገቱ ሲወሳ ኢትዮጵያ ማለት 80 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆን አይዘንጋ፤ በቤተመንግስት ዙሪያ በተሰባሰቡት ጥቂት ሺዎች የኑሮ ደረጃ የኢትዮጵያ ስታስቲክስ አይሰራ፤ ዕውነቱን እንጋፈጥ፤ ለምን መራመድ አቃተን? ለምንስ ተስፋ ራቀን? ለምንስ አቅም አነሰን? ይህንን መፈተ ሹና ለተግባራዊነቱ በቅንነት፣ በኃላፊነት መንቀሳቀሱ ተገቢ ነው፤ነጻነትና ዕኩልነት የስኬት ወሳኝ ግብአት (input} መሆናቸውም አይረሳ፤ከህዝብ ጋር የሚፈጠር መተማመንም መንገዱን ለስላሳ ፍሬውንም ጣፋጭ ያደርገዋል::

**ለአስተያየትም እነሆ ኢሜል**

lualawi2000@yahoo.com

ነሃሴ 1/2002